የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 37
ADDIS ABABA 15th May, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፴/፪ሺ፩ ዓ.ም

ለውቅሮ-ዛላአምበሳ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ ኤኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፴

CONTENTS

Proclamation No. 630/2009

Kuwait Fund for Arab Economic Development Loan Agreement for Financing the Wukro-Zalambesa Road Project Ratification Proclamation Page 4730

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፴/፪ሺ፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለውቅሮ-ዛላአምበሳ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፯ሚሊዮን /ሰባት ሚሊዮን/ የኩዌት ዲናር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፳፰ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለውቅሮ-ዛላአምበሳ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 630/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE KUWAIT FUND FOR ARAB ECONOMIC DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development stipulating that the Kuwait Fund for Arab Economic Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of seven million Kuwaiti Dinars (KD 7,000,000) for financing the Wukro Zalambesa Road Project, was signed in Addis Ababa on the 28th day of October 28, 2008.

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 30th day of April, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited a the "Kuwait Fund for Arab Economic Development Loan Agreement for Financing the Wukro-Zalambesa Road Project Ratification Proclamation No. 630/2009".

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፳፰ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 774 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፯ሚሊዮን /ሰባት ሚሊዮን/ የኩዌት ዲናር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement No. 774 signed on October 28th, 2008 at Addis Ababa between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 7,000,000 KD (seven million Kuwaiti Dinars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**